# መደመር ሲሉ መደመር ስንል

ሐምሌ 26 ቀን 2010ዓም(02-08-2018)

መደመር የሚሉት ቃል በጆሮ ሲሰማ መልካም ነው፤ስሜትን ይስባል።መደመር ከነጠላነት ወደ ብዙነት ፣ብዛት ደግሞ ከደካማነት ወደ ጠንካራነት መሸጋገር ማለት ነው። መደመር በሁሉም አቅጣጫ ለጋራ ውጤት ምክንያትና መሰረት ይሆናል።ለጥፋት የአጥፊዎች መደመር እንዳለ ሁሉ፣ ለልማትም የአልሚዎች መደመር ይኖራል።

አንድ ቤት ለመስራት የብዙ የግንባታ መሳሪያዎች መደመርን ወይም ውህደትን ይጠይቃል።መልካምና አስተማማኝ ቤት ለመስራት የመሳሪያዎቹ ወይም የግንባታ ምርቶቹ ጥራትና ጥንካሬ ወሳኝ ነው።በማይረባ መሰረት ላይ ጥራት የሌላቸውን ቁሳቁስ(material) አሰባስቦ ወይም ደማምሮ ግንባታ መጀመሩ ከድካሙ በላይ አደጋው ከፍተኛ ነው።

በምግብ በኩልም የተለያዩ ማዕድናትንና (ንጥረ ነገሮችን) የያዙ ለጤና የሚጠቅሙ የእህል ዘሮችን አቀላቅሎ በዘመኑ አባባል ደማምሮ ማዘጋጀቱ ትልቅ ጥቅም አለው።አንዱ የእህል ዘር የሌለው ቫይታሚንና ፕሮቲን ሌላው ስለሚኖረው ቢደመሩ ወይም ቢቀላቀሉ ለተመጋቢው የተሟላ ጥቅም ይኖረዋል።

በመደመር ወይም በመቀላቀል ስም መርዛማና ጎጂ ውጤት የሚኖረውን፣ እህልና እንክርዳዱን ወይም የነቀዘውን በአንድ ቅርጫት ውስጥ እናስቀምጥ ቢሉት የምግብነት ጥራቱ ይወርዳል፣ተመጋቢውን ለብዙ በሽታ ይዳርጋል። ከሚሰጠው የምግብነት ጥቅም ይልቅ መርዛማ ጉዳቱ ያመዝናል።ለዚያም ነው እህልን በንጽህና ለማዘጋጀትና የምግብነቱን ጥራት ለመጠበቅ ከመቀላቀሉ በፊት የሚለቀመውና በወንፊት የሚበጠረው። ቀጥሎም የቱ ከየትኛው ጋር ቢቀላቀል የሚኖረውን ጥቅምና ጉዳቱን በቅድሚያ መረዳት ያስፈልጋል።የተበጠረ እህል ከተበጠረ ሌላ የእህል ዘር ጋር ቢቀላቀል ጤናና ጉልበት ይሰጣል።በሽሬታው(በመጠኑም) ከፍ ስለሚልም ለረጅም ጊዜ ለብዙ ቤተሰብ ፍጆታ ብቃት ይኖረዋል,።

መደመርን ከግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች አኳያ ካዬነው በቅድሚያ የተደማሪዎቹን ማንነትና ምንነት ማወቁ ውጤቱን ይወስነዋል። በዚህ የመደመር ሂደት የሚደማመሩት አካሎች በምግባር፣በጸባይ፣በአቋምና በዓላማ የማይመሳሰሉ ከሆነ፣እንደመር ብለው ቢነሱ ውጤቱ መደመር በሚያመጣው መደናበር፣ ጉዳት፣ግጭትና ኪሳራ ውስጥ መነከር ይሆናል።

መደመር እንደ ጥቅሙ ጉዳትም ይኖረዋል።ለብዛት ብቻ ተብሎ የሚደረግ ጥራት ያልጠበቀ ድምር ይዞት የሚመጣው ጉዳት ከመደመር በፊት ከነበረው ጉዳት እጅጉን ያመዝናል።በፖለቲካው ዓለም መደመር የተለመደ ነው።ግንባር፣ቅንጅት፣ጥምረት...የሚሉት ፈሊጦች ሁሉ የዛው የመደመር ጽንሰሃሳብ ውጤቶች ናቸው።የግንባሮች መፈራረስ መነሻው የተደማሪዎቹ ምንነትና ዓላማ የሚያስከትለው ልዩነት ነው።ለጥንካሬውም እንዲሁ።በነዚህ የመደመር ሂደት ውስጥ ግን የመቀነስ ተግባርም ይከናወናል።በመደመር ስም አንዱ ሌላውን አዘናግቶ የማጥፋትና የማሶገድ ሴራ ይጎነጎንበታል።መደመር፣መተባበር፣አንድ መሆን...ወዘተ የሚሉት አንዱ ሌላውን ተጠግቶ፣ደካማ ጎኑን ተረድቶና አዘናግቶ ለማጥቃት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩበት ዘዴ እንደሚሆን ከታሪክ መረዳት ይቻላል።

በግምባር ስም፣በመደመር ስም አንዱ ሌላውን አቅርቦ ሲያሶግደውና እንዳያንሰራራ አድርጎ ሲያጠፋው በታሪክ ታይቷል።በያገሩ ያየነው ግጭት አብዛኛው በአንድ ወቅት ግንባር መስርተው፣ተደማምረው በተጠጋጉ ሃይሎች መካከል፣ አንዱ ሌላውን አጥፍቶ የበላይ ለመሆን በሚፈጠረው ችግር የመጣ ነው።በዚያ የከይሲዎች ሴራ ግን የሚጎዳውና ለችግርና ስቃይ የሚጋለጠው ሰፊው ሕዝብ ነው።አገርም ይፈራርሳል።

አሁን ላለፉት 27 ዓመታት አገራችንን በጎሳ ከፋፍሎ የሚያምሰው የህወሃት ቡድን ገና ከጅምሩ ጫካ ውስጥ እያለ በእንደመር ሃሳብ አታሎ አጥቅቶበታል። አምነውት የተሰባሰቡትን ቡድኖች በተኙበት ቦታ ላይ በጥይት ደብድቦ መፍጀቱን በህይወት የተረፉት የሚመሰክሩት ነው።የዚያው ሴራ ፈጻሚ የሆኑት አሁንም በመደመር ስም፣ ሌሎቹን አታለውና አነሁልለው ሲያፋጁ እንደኖሩት ሁሉ አሁንም ለማፋጀት ሴራ በመጎንጎን ላይ ናቸው።

ኢሕአዴግ የተባለው የዚሁ የህወሃት የመደመር ውጤት የሆነው ግንባር ላለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የፈጸመው ወንጀል በሕዝብ ትግልና መስዋእትነት አሁን ወዳለበት የመውረግረግ ደረጃ ላይ አድርሶታል።በውስጡ ይዟቸው የነበሩት የወንጀሉ ተካፋይ የሆኑት የግንባሩ አባላት በሕዝቡ የትግል ማዕበል ተገደው ካምፓቸውን ሙሉ ለሙሉ ባይለቁም የሕዝቡን ፍላጎት የሚያንጸባርቁ(አምነውበትም ሆነ ለስልታዊ )እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆናቸውን ላለፉት ሶስት ወራት አይተናል።በግምባር ቀደምትነት የዚህ ሂደት አስተናጋጅ የሆኑት የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት(ኦሕዴድ)፣የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ብአዴን)መሪዎች ሲሆኑ፣ጥቂቶቹም ተባብረዋል። ሌሎቹም የኢሕአዴግ አባል ድርጅት አመራር አባላት ፈራ ተባ እያሉ፣ ጅዋ ጅዌ እየተጫወቱ ነው። በመደመርና በመቀነስ መሃል እየዋዠቁ ይገኛሉ።በሰሩት ወንጀል የማይጠዬቁና የሕዝቡም ትግል ማሸነፉን ካመኑ ተደምረናል ብለው መምጣታቸው አይቀርም።ያ እስኪሆን ድረስ ግን ለማሰናከል የማይገለብጡት ድንጋይ አይኖርም።

በነዶር አብይ የሚመራው የመደመር እንቅስቃሴ ለጆሮ የሚጥሙ ዲስኩሮችን በማሰማቱና አንዳንድ መሰረታዊ ያልሆኑ ለውጦችንና ያሰራር ልምዶችን በማሳየቱ ብዙ ሕዝብ ደግፎትታል፤ እምነትም ጥሎበታል።የታሰረው ሲፈታ፣መሪ በስብሰባ ከሕዝብ ጋር ሲወያይ ማዬት እራሱን የቻለ ለውጥ በመሆኑ የዚህን አይነት የሕዝብ ስሜት ማዬቱ የሚጠበቅ ነው።

በቅርቡም በአሜሪካ በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይአገር አቋርጦ የተገኘው ኢትዮጵያዊ የተስፋና የፍቅር፣ የአንድነትና የሰላም ናፍቆት ስላለበት ያንን የሚያበስሩ ቃላቶች በመስማቱ ደስታውን ከንግግር በፊት በሚያሰማው ጩኸት፣ እልልታና ጭብጨባ ገልጿል።እንኳንስ ተራው ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት አለን፣ሕዝብን እንመራለን ብለው ሲያወሩ የነበሩት የድርጅት መሪዎች ሳይቀሩ እጃቸውን የሰቀሉበት ሁኔታ ነው።ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ ከመወያዬትና ጥያቄ ከማቅረብ ይልቅ እራሳቸውን በማስተዋወቁና እነዶር አብይን በማወደሱ ተግባር ላይ ተጠምደው የታዩበት ወቅት ነበር።በአገር ቤት የሚከታተለው ሕዝብ በውጭ ባሉት የተቃዋሚ ድርጅቶች ያፈረበት ጊዜ መሆኑ በተላለፉት መልእክቶች ለማወቅ ተችሏል።እርግጥ እነዶክተር አብይ እስከአሁን ላደረጉት ማመስገን ተገቢ ቢሆንም ብዙ ኢትዮጵያዊ መስዋእት የከፈለበት የትግል ውጤት መሆኑን መዘንጋት ስህተት ነው።

የአገራችን ሰላምና አንድነት አሁንም አደጋ ውስጥ ነው።አሁንም ፖለቲካው የሚሽከረከረው በጎሳ መዘውር ነው። እነዶር አብይ አሁንም ኢሕአዴግ የተባለው የጎሰኞች ግንባር አባላት እንጂ ከዚያ የወጡ አይደሉም።አሁን የሚያደርጉት ሁሉ የኢሕአዴግን መጠናከር ያሳያል ሲሉም በአደባባይ ተናግረዋል።እነዶር አብይ መደመር ሲሉ ኢሕአዴግ የቀደደውን የጥገና ጎዳና ተከተሉ፣ያለውን አገር የሚበታትን ሕገመንግሥት (ሕገአራዊት ማለት ይቀላል)ተቀብላችሁ ተንቀሳቀሱ ማለት ነው።በነዶር አብይ የድመራ ስሌት ሁሉም አመራራቸውን ተቀብሎ የሂደቱ አካል ሆኖ ይሂድ ማለት ነው።ሁሉም የሚጠይቀው የሽግግር ወቅትና ሁሉን አቀፍ የመግባባት ጉባኤ ዋጋ የለውም ብለዋል።እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ላለው የሁለት ዓመት ጊዜ እነሱው አሻጋሪና ወሳኝ እንደሆኑ ዶር አብይ በግልጽ ተናግሯል።ሕዝብ የሚጠይቀውን አልቀበልም ማለት ደግሞ የአምባገነንነት አቋም መያዝ ይሆናል። የአሁኑን የለውጥ ሂደት ያመጣው የሕዝብ ትግል እንደመሆኑ ለሚቀሩትም ጥያቄዎች መመለስ የሕዝቡ ትግል ወሳኝ ነው።በመደመር አባዜ እንዳይኮላሽ መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

አሁን የተያዘው የመደመር ፈሊጥ  የዘረፈ፣የገደለ፣አገር የመዘበረ፣ሕዝብ ያፈናቀለ፣ አገር ያስደፈረና ድንበር አፍርሶ መሬት ቆርሶ የሸጠ፣ልዩ ልዩ ወንጀል የፈጸመ ሁሉ በፍቅርና በይቅርታ ስም ሳይጠዬቅ በሰላም ይኑር ማለት ነው። ይህንኑም ዶር አብይ አህመድ ቀደም ሲል"ሂሳብ መወራረድ የለም" በሚለው መሪ ቃል አጠቃሎታል።

የዶር አህመድ መደመር ማለት በብዙ ወንጀሎች የሚጠረጠሩትንና ሕዝቡ ይቀጡ የሚላቸውን በስልጣን የባለጉ ሰዎች በሹመትና በእረፍት ስም ወደ ውጭ እንዲሄዱ ማድረግ፣ከአንዱ  የሥልጣን ቦታ ወደ ሌላው ማዘዋወር፣ በጡረታ ስም ገለል እንዲሉና በዘረፉት ገንዘብ አማካኝነት ቅስቀሳ በማድረግ  ያንኑ መርዛማ ተንኮላቸውን እንዲረጩ ዕድል መስጠት፣አንዳንዶቹንም እንደ ንጹህ ዜጋ አጃቢዎቹ ማድረግ  እንደሆነ አይተነዋል ይህም በመሆኑ በአገር ቤት ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "አልደመርም" የሚል ድምጽ እያስተጋባ መጥቷል።ነገ ደግሞ በውጭ አገር በሚኖረው ሳይደመጥ አይቀርም።አልደመርም ከሚለው ይልቅ ድምሮሹ ትክክለኛና ለእውነተኛ ለውጥ በሚያበቃ  መልኩ  ቢሆን  ይመረጣል።

 የሕግ የበላይነትና ፍትሕ ሲረገጥ እያዩ በመደመር ስም እያጨበጨቡ ለውጥ መጣ ማለት  ጸረ ፍትሕ መሆን ማለት ነው።ከወንጀለኞች ጋር መደመር ማለት ነው። አጥፊ ሳይለይ ለዳግመኛ ጥፋት ይዘጋጅ ማለት ነው።ያ ደግሞ  ከሕግ ጋር መጣላትና ከፍትሃዊ ስርዓት መቀነስ ማለት ነው። አጥፊና ጠፊ አብሮ አይሄድም።በአገራችን ባህል ያጠፉ ይቀጣል፤ለተበደለ ካሳ ወይም ጉማ መክፈል የተለመደ ነው።ሰው በጥፋቱ ይቀጣ ሲባል የጭካኔና የአውሬነት አቋም ማስተናገድ የሚመስላቸው ይኖሩ ይሆናል።ያማ ባይሆን ኖሮ ሕግና የፍትህ ተቋማት ባላስፈለጉም ነበር። የጥፋት  ዋጋ መክፈል እንዳለበት በፈጣሪ ቃል በሆነው በመጽሃፍ ቅዱሱም ሳይቀር  የተገለጸ ነው።አምላክ አዳም ለምን እንደሞተ ሲያስረዳ "የሃጢያት ዋጋ ሞት ነው" ሲል የሰው ልጅ ለሰራው ሃጢያት በሞት እንደሚቀጣ ሕግ አስቀምጧል፤ለዚያም ነው ሁላችንም የምንሞተው።

ባለፈው ጊዜ ወንጀል የፈጸሙ ባለመጠየቃቸው "ማን እንደተጠዬቀ እጠየቃለሁ" በሚል እብሪት  እንደ መከላከያ ሆኖ ለዛሬዎቹ ወንጀለኞች የልብ ልብ ሰጥቷቸዋል።ለወደፊቶቹም ወንጀለኞች ማበረታቻ ይሆናል። ከዚህ አይነቱ ድክመት ለአንዴና ለሁለዬው መላቀቅ አለብን።ለመጭው ትውልድ የፍትሕን ትርጉም በተግባር  ልናስተምረው ይገባል።በፍቅርና በይቅርታ ወይም በእርቅና መግባባት ወይም  በመደመር ሽፋን ልንጨፈልቀው አይገባንም። ለወደፊቱ ሕጋዊ ስርዓት አሁን ሕግን  የማክበርና የማስከበር ሥራ የሕግን ተቋም በማጠናከር መጀመር አለብን። መንግሥቱ ሃ/ማርያም ሳይቀር በመደመር ስም በጨፈጨፈው ሕዝብ ፊት ቀርቦ ሳይፈረ,ድበት ስሙን እያነሱና አቅፈው ፎቶ በመነሳት የይቅርታ ተምሳሌት ለመሆን መሞከር የወንጀሉ ደጋፊ ከመሆንም በላይ በብዙ መቶ ሽህ ለሚቆጠሩ ተጠቂዎችና ቤተሰቦቻቸውም ንቀት ነው።ለፍትህም ደንታ ቢስነት ነው።የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ይህንን ድርጊት ሲፈጽም በመንግሥት እውቅና የተሰጠው  ቢሆንም ባይሆንም በዶር አብይ በሚመራው መንግሥት ላይ ግን ጥቁር ነጥብ ማስቀመጡ አይቀርም።የደጋፊውን ቅስም ይሰብራል።

ከላይ በእህልና በቤት ግንባታ ምሳሌ እንደተገለጸው የመደመሩ(የመቀላቀሉ፣የአብሮ የመቆሙ፣የመጠንከሩ...)ፍላጎት የተሳካና ዘላቂነት የሚኖረው ለዚያ ጠንክ የሚሆኑትን ለይቶ ማውጣቱና የሚገባቸውን የፍትህ ውሳኔ እንዲያገኙ ሲደረግ ነው።የመለያዬቱ ግምብ ፈርሶ(ተቀንሶ) የመገናኛው ድልድይ የሚገነባው (የሚደመረው)ጥራትና ጥንካሬ ባለው ቁሳቁስ ትብብር እንጂ በቆሻሻ ክምር አይደለም።

የአገር ወዳዶቹ ኢትዮጵያውያን የመደመር ትርጉም፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑት፣ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት የቆሙ፣ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን የሚታገሉትን ፣የጎሳ ፖለቲካ የሚያራምዱትን ቡድኖች  ኢሕአዴግን ጭምር የሚቃወሙ፣ሰብአዊና የዜግነት መብት እንዲከበር የሚታገሉትን ደምሮ የሚያስተሳስርና የሚያጠናክር ነው። አሰስና ገሰሱን፣ ወንጀለኛና ወንጀል የተፈጸመበትን፣ገዳይና ተገዳይን፣አፈናቃይና ተፈናቃይን ፣ዘራፊና ተዘራፊን። ጎሰኛና ከፋፋይን፣ጅሃዲስቱን ጭምር በአንድ ድንኳን ውስጥ የሚጠቀጠቅበት አባዜ ማለት አይደለም።

አገር ወዳዶቹ የራሳቸውን የድምር ውጤት ይዘው ብቅ ሊሉ ይገባል።በኢሕአዴግ የድመራ ሰንጠረዥ ውስጥ ለመግባት መራኮት የለባቸውም።

በመደመር ስም ተግበስብሶ መሄዱ አሁን ግንባር ቀደም በሆኑት የለውጥ ሂደት መሪዎች ላይ አደጋ አለው።የሰኔ 16 ቱ የሽብር እርምጃ አንዱ ምሳሌ ነው።ዶር አብይና ሌሎቹ እራሳቸውን ለማዳንና የቆሙለትን የሕዝብ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በከባቢያቸው ያለውን ፈንጂ ደፍረው ሊያጸዱ ይገባቸዋል።ያ ፈንጂ የሚዘጋጀው ደግሞ በኢሕአዴግ ውስጥና ውጭ ያሉት ጸረ አንድነትና ለግል ስልጣንና ጥቅም በቆሙ ሃይሎች ነው።ለዚያ ዘመቻ ትልቁ መሳሪያቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው።በተጨማሪም ጠንካራ የመንግስታዊ መዋቅር/ተቋማት (institutions)መኖርና ለዚያ ተገቢ ሙያተኞችን (በጎሳ ሳይሆን በብቃት) መመደብ ወሳኝነት አለው። በዚህ የመደመርና የመቀነስ ስሌት ከተንቀሳቀሱ እራሳቸውንና አገራችንን ከተደቀነባት አደጋ ማዳን ይችላሉ።ፈንጂ ወረዳ ውስጥ ሆኖ መደመር መደመር ቢሉት ውጤቱ መቀነስ ይሆናል።

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!

አገሬ አዲስ